- ትርጉም ከጀርመንኛው -

ጥቅምት 19 ቀን 2013 ዓ.ም

**ክቡራትና ክቡራን**

እ.ኤ.አ. በጁላይ ወር 2020 ዓ.ም ለቻንስለር ዶ/ር አንገላ መርከል በጻፍነው ግልጽ ደብዳቤ **በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ** ግድብ ሙሌት ዙሪያ የወጣ የተዛባ ሪፖርት ላይ ያለንን ስጋት ገልጸናል። ደብዳቤው በጀርመን በሚኖሩ 60 ኢትዮጵያውያን እና ጀርመን-ኢትዮጵያውያን፣ የተቋማት፣ የኮሚኒቲዎችና የማህበራት ተወካዮች፣ የተለያዩ ትምህርቶች አካዳሚሻን፣ አርቲስቶች እና ኢንተርፕሩነሮች የተፈረመ ነው።

ይህ ከሆነ የተወሰነ ጊዜ ያለፈ ሲሆን፣ የታላቁ የህዳሴ ግድብ የመጀመሪያ ሙሌትም በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል። እስካሁንም በሱዳንና በግብጽ ሊከሰት ይችላል የተባለው ስጋት ሳይፈጠር ቀርቷል። በተቃራኒ ሱዳን እ.ኤ.አ. በሴፕቴምበር 2020 ዓ.ም የከፍለ ዘመኑን ጎርፍ አይታለች። እንደ ተ.መ.ድ የሰብዓዊ ዕርዳታ ማስተባበርያ ቢሮ የዓባይ ወንዝ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ በ17.5 ሜትር ከፍተኛውን የውሃ ከፍታ ደርሷል። በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ መያዝ በተቻለው የ4.9 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውሃ ምክንያት ሊደርስ የሚችለው ጥፋት ቀንሷል።

የአየር ንብረት አጥኝዎች በዓለም ሙቀት ምክንያት በምስራቅ አፍሪካ የዝናብ መጠን እየጨመረ መሆኑን ታዝበዋል። በመሆኑም ግድቡ በቀጣይ በሱዳን ሊኖር የሚችልን ጎርፍ በመከላከልና ማስተካከል ረገድ ዋነኛ ሚና ይጫወታል። የግድቡ ጠቀሜታ በተለይ በሱዳን ለሚገኙ ህብረተሰቦች ግልጽ የሆነ መሆኑና በኔቸር ገለልተኛ አጥኝዎች በቅርቡ በስፋት የተሰራጨ ጥናት (https://www.nature.com/articles/s41467-020-19089-x) ግድቡ ግብጽ ላይ ጉልህ ጉዳት ሳያደርስ ሱዳን እና ኢትዮጵያን እንደሚጠቅም አሳይቷል። በኢትዮጵያ የግድቡን ግንባታ ለማጠናቀቅ የሚሰራው ሰራ መልካም ለውጥ እያሳየ ነው። በግድቡ ዙሪያ በግብጽ የሚታየው አመለካከትም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አዎንታዊ ለውጥ እየታየበት ነው።

ሆኖም ግን የወቅቱ የአሜሪካ ፕሬዘዳንት ዶናልድ ትራምፕ ባደረጉት ንግግር ተደናግጠናል። እ.ኤ.አ. ኦክቶበር 23 ቀን 2020 ዓ.ም ከእስራኤልና ሱዳን መንግስታት መሪዎች ጋር በነበራቸው የስልክ ውይይትና በተለያዩ የሚዲያ አውታሮች በስፋት በተሰራጨ ቪዲዮ ስለ ግድቡ የተናገሩ ሲሆን፣ በንግግሩም ግድቡ ወደ ግብጽ ውሃ እንዳይሄድ የሚያደርግ በመሆኑ **ግብጽ ግድቡን ማፈንዳት አለባት** ብለዋል። ቃል በቃል፤ *"It is a very dangerous situation because Egypt is not going to be able to live that way. They'll end up blowing up that dam [...] I say it loud and clear, They'll blow up that dam,"* (የንግግሩን የዩትዩብ ማገናኛ ( 'ሊንክ' ) በዚህ ማግኘት ይችላሉ፤ https://youtu.be/XSxvCd7af-c).

ለኤሌትሪክ ማመንጫ የሚያገለግል ግድብ ሥራውን ለመፈጸም የግዴታ ውሀ መልቀቅ (ማሣለፍ) አለበት፣ ፕሬዘዳንት ትራምፕ ይህን የመሠለ ሀቅ እና ብዙ ሁኔታዎችን ያለተረዱ መሆናቸው ግልጽ ነው።

ግድቡ የቀጠናውን የውሃ አቅርቦት በሂደት የሚያሻሽል መሆኑ ላይ ኤክስፐርቶች ይስማማሉ። በ2020 ዓ.ም የነበረው ከባድ ዝናብ ኢትዮጵያ የመጀመሪያዋን የሙሊት ደረጃ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንድታሳካ አስችሏል።
ኢትዮጵያ ምክንያታዊ አጠቃቀምና ከፍተኛ ጉዳት በማያስከትሉ የፍትሃዊነት መርሆችን በማክበር የህዳሴ ግድብን የመሙላት እና የመጠቀም መብት አላት፡፡ ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ለአባይ ውሃ 86% የምታበረክት ቢሆንም ከ65

ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያውያን የኤሌክትሪክ ሃይል ተጠቃሚዎች አይደሉም፡፡ ነገር ግን 98% ግብፃውያ የኤሌክትሪክ ሃይል ተጠቃሚ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ እንደግብፅ ከፍተኛ መጠን ያለው የከርሰምድር ውሃ እንዲሁም የባህርን ውሃ ከጨው በመለየት ለመጠቀምም ባህር ስለሌላት አትችልም፡፡ የአብዛኛው የኢትዮጵያ ሃይል የሚመነጨው 'ከባዮማስ' (ከአንጨት) በመሆኑ፣ ይኸም የደን መመንጠርን ፣ የአካባቢን (Environment) እና የመሬት መጎሳቆልን ፣ድርቅ ፣ ጎርፍና ረቂቅ የእንሰሳትና የሰው በሽታን ያስከትላል። በአየር ንብረት ለውጥ እና በተዛባ ዝናብ ምክንያት ቁጥራቸው ወደ 8 ሚሊዮን ያህል ሰዎች በየአመቱ ለአስቸኳይ የምግብና ሰብአዊ ድጋፍ ጥገኞች ሆነዋል። ለኢትዩጵያ የግድቡ መገንባት እና የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጨት ቅንጦት ሳይሆን ከሞት የሽረት ያህል አስፈላጊ ነው፡፡ በፍጥነት እያደገ ያለውን የህዝብ ብዛትና በአሁኑ ሰዓት ከ110 ሚሊዮን በላይ የሆነውን ህዝብ ከከፋ ድህነት ለማውጣት ግድቡ ለኢትዮጵያ ወሳኝ ነው፡፡ ኢትዩጵያ ባልፈረመችው ፣ በቅኝ ገዥዎች በተፈረመ ውል መሠረት ግብጽ የአባይን ውሀ ለመቆጣጠር የይገባኛል ደረቅ (ፍንክች የማይል) ጠንካራ አቋም ታሣያለች።

ግብጽ በግድቧ ውስጥ በጣም ብዙ ውሀ አላት፣ በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ የአስዋን ግድብ ውስጥ የተመዘገበ 40 ቢሊዬን ኪዩቢክ ሚትር ያህል የውሀ ክምችት ይገኛል።

የፕሬዚዳንት ትራምፕ አስተያየትም በሁሉም ደረጃ ላይ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን ከፍተኛ ስጋት እና ቁጣ የቀሰቀሰ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብና እኛ ፈራሚዎቹም እንደዚህ ዓይነት በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ላይ የሚሰነዘሩ ዛቻዎች የተሳሳቱ፣ ፍሬያማ ያልሆኑ እና የዓለም አቀፍ ህግን የሚጥሱ ናቸው ብለን እናምናለን፡፡ የፕሬዚዳንቱ መግለጫ በኢትዮጵያ እና በአሜሪካ መካከል ያለውን ከመቶ ዓመት በላይ የሆነውን የረጅም ጊዜ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትን አያንጸባርቅም ፡፡

ይህንን ደብዳቤ ለእርስዎ ስናቀርብ አሁን እየተከናወነ ያለውን ሁኔታ ትኩረት እንድትሰጡትና ድርድሩን ወደ መጨረሻ የሚወስድ ሚዛናዊ አቋም ላይ እንዲደረስ ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ የጀርመን ፌደራላዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና የአውሮፓ ህብረት ገንቢ ለሆነው ትብብርና ለብሔራዊ ሉአላዊነት ክብር ያደረጋችሁትን ሁሉ እናመሰግናለን። ከዚህም በተጨማሪ የጀርመን ፌደራል ሪፐብሊክ መንግስትና የአውሮፓ ህብረት በአሁኑ ወቅት የኮቪድ-19 ወረርሽኙን ለመዋጋትና ለልማት ላደረጋችሁት ድጋፍ እናመሰግናለን፡፡ በመጨረሻም ለጀርመን የመገናኛ ብዙሃን ሚዛናዊ ዘገባም እንዲሁ እናመሰግናለን፡
፡

ከከበረ ሠላምታ ጋር

*[ፈራሚዎች]*

ፕሮፌ. ዶ/ር አስናቀች ላስ-ስዩም ፣

በቴክኒካል ኬሚስትሪ ፕሮፌሰር፣ በርሊን፤
በኢትዮጵያ ባሌ የትምህርት ቤቶች ከፍተኛ አስተባባሪ፣
ከአዲስ አበባ የቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በዕቀውቀት
ሽግግር ዙርያ በተለይ በኢነርጂና ታዳሽ ኃይል ላይ የሚሰሩ

ዶ/ር ጺጋዬ ደግነህ

ኢኮኖሚስት፣ በጀርመንና ኢትዮጵያ መካከል የዕውቀት ሽግግርና፣በትልቅ ኮርፖሬሽን የህብረ-ብሄራዊነት አስተዳደር ላይ የሚሰሩ፣ በዓለምአቀፍ ስፖርት ማህበር የስነ-ምግባር ኮሚሽን ምክትል ፕሬዝዳንት

**አድራሻ፤**

ፕሮፌ. ዶ/ር አስናቀች ላስ-ስዩም፣
Klingerstr. 2, 1243 Berlin, Deutschland
ኢሜይል: Asnakech.Lass-Seyoum@HTW-Berlin.de
ስልክ: +49 177 8726581

**አድራሻ፤**

ዶ/ር ጺጋዬ ደግነህ
Taylorstr. 9B, 14195 Berlin, Deutschland
ኢሜይል: mail@degineh.de
ስልክ: +49 177 46 26 050

**(-German-English Translation–)**

October 29, 2020

Dear Sir or Madam,

In July 2020 we expressed our concern about the misleading reporting in connection with the filling of the **Grand Renaissance Dam (GERD)** in Ethiopia in an open letter to Chancellor Dr. Angela Merkel. The letter was signed by 60 Ethiopians and German-Ethiopians living in Germany, representatives of organizations, communities and associations, academics of various disciplines, artists and entrepreneurs.

Some time has passed since then and the first filling of the GERD has been successfully completed. So far the feared water shortage for Sudan and Egypt has not occurred. On the contrary, Sudan experienced a flood of the century in September 2020. According to the UN Office for the Coordination of Humanitarian Aid, the Nile reached the highest water level in living memory at 17.5 meters. The 4.9 Billion Cubic Meter (BCM) stored in the GERD has helped to lessen the blow.

Climate researchers observe that global warming is resulting in increased precipitation in East Africa. The dam will therefore make a major contribution to regulating floods and preventing flooding in the Sudan in future. The benefits of the dam have thus become clearer, especially to the population in the Sudan. A recent widely circulated study by the Nature from independent researchers (https://www.nature.com/articles/s41467-020-19089-x) showed the benefit for BOTH Sudan and Ethiopia without significantly impacting Egypt. In Ethiopia, the construction work to complete the dam is now making a good progress. The attitude towards the dam in Egypt has also improved recently.

However, we are currently shocked by a statement made by the incumbent President of the United States of America, **Donald Trump**. On 23rd of October 2020, during a telephone conversation with the leaders of the states of Israel and the Sudan, which was circulated in the various media, he also spoke about the dam. He mentioned that the dam would not allow any more water to enter Egypt, thus **Egypt would have to blow up the dam**. Literally he said: "It is a very dangerous situation because Egypt is not going to be able to live that way. They'll end up blowing up that dam [...] I say it loud and clear, They'll blow up that dam," (you can find the link of the conversation on YouTube: https://youtu.be/XSxvCd7af-c).

President Donald Trump is obviously unaware of many aspects, such as the fact that a dam used to generate electricity must let water through to perform its function. Experts agree, that the dam will improve the region's water supply in the long run. In 2020, heavy rainfall enabled Ethiopia to achieve the first phase filling in very short time.

Ethiopia has the right to fill and operate the GERD by complying with the principles of equitable and reasonable utilization and the obligation not to cause significant harm. Though, Ethiopia contributes 86% of the Nile water, over 65 million Ethiopians do not have access to electricity, while 98% Egyptians have access to electricity. Ethiopia does not possess a significant amount of ground and sea water for desalination as Egypt does. Most of Ethiopia's energy is derived from biomass resulting in deforestation and environmental and land degradation causing flood,

draught, animal and human disease. Due to climate change and erratic rain, about 8million people in Ethiopia depend on emergency Humanitarian food assistance every year. Building the dam and generating energy is not luxury for Ethiopia, actually it is a grave necessity. Ethiopia needs the dam to lift its rapidly growing population (which now more than 110 million) out of extreme poverty.

Egypt shows lack of flexibility and a strong claim to control Nile water as per the colonial treaty to which Ethiopia is not a signatory. Egypt has a lot of water in its High Aswan Dam and there is currently a record amount stored.

President Trump's comments were received with great concern and outrage by Ethiopians from all social classes. The Ethiopian people - and we, the signatories, also - believe that such threats and insults to Ethiopian sovereignty are misguided, unproductive and clear violations of international law. The president's remarks do not reflect the long-standing diplomatic relations between USA and Ethiopia that has existed for more than 100 years.

With this letter, we would like to bring to your kind attention the ongoing situation with a view to achieve balanced stance that will eventually lead to a negotiated outcome.
We would like to take this opportunity to thank the government of the Federal Republic of Germany and the European Union for their constructive cooperation in full mutual respect and with respect for national sovereignty. We would also like to thank the Federal Republic of Germany and the European Union for the current support in the fight to against Covid-19 and for continued development assistance. Our thanks also go to the German media for their balanced reporting.

With best regards,

**Prof. Dr. Asnakech Laß-Seyoum**

[Signed]

**Frau Prof. Dr. Asnakech Laß-Seyoum,**
Professor of Technical Chemistry, Berlin, lead coordinator of school projects in Bale Ethiopia, knowledge transfer with the University of Technology in Addis Ababa with a focus on energy technologies and renewable energies

**Dr. Tsegaye Degineh**

[Signed]

**Herr Dr. Tsegaye Degineh,**
Economist, knowledge transfer Germany-Ethiopia, diversity management at a large corporation, i.e. Vice President of the Ethics Committee of an international sports association

**Contact:**

Prof. Dr. Asnakech Laß-Seyoum,
Klingerstr. 2, 1243 Berlin, Deutschland
Email: mail@asnakechlass-seyoum.de
Tel: +49 177 8726581

Dr. Tsegaye Degineh,
Taylorstr. 9B, 14195 Berlin, Deutschland
Email: mail@degineh.de
Tel: +49 177 46 26 050